## ፍኖተ ስቀል

ከሊቶስጥራ /የጲላጦስ አደባባይ ተነስቶ መስቀሉን ተሸክሞ መከራውን ታግሶ እስከ ቀራንዮ የተጓዘበት ፍኖተ መስቀል ይባላል። ላቲኖች ጌታ በጲላጦስ ፊት ከቆመበት ቦታ ጀምሮ እስከ መካነ መቃብሩ ድረስ በእለተ አርብ የሆነውን ሁሉ እያነበቡና እየተረኩ ወደ ላይ ወደ ቀራንዮ ይገባሉ። በየጉዞው ላይ ጸሎት የሚያደርሱባቸው 15 ምዕራፎች አሉ።

### የመስቀል ጉዞ ምራፍ




የመጀመሪያዎቹ አምስት ምዕራፎች ከጲላጦስ አደባባይ እስከ ስምኦን ቀሬናዊ የጌታን መስቀል እስከተሸከመበት ያለውን ያካትታል እነሱም፡-

- ምዕራፍ 1. የጲላጦስ አደባባይ በዕብራይስጥ ገበታ ሲባል በግሪክ ሊቶስጥራ ይባላል። የሞት ፍርድ የተላለፈበት ቦታ ነው (ፍትሀ ሞት ላዕለ ክርስቶስ)
- ምዕራፍ 2. ጌታ የተገረፈበት፡- ጲላጦስ ጌታን ገርፎ ያ ሰው ያውላችሁ ያለበት ቦታ።
- ምዕራፍ 3. ጌታ በመጀመሪያ የወደቀበት ቦታ (ወዲቀ ምድር ቀዳማዊ)
- ምዕራፍ 4. እመቤታችንን ልጇን ያገኘችበት ቦታ
- ምዕራፍ 5. ቀሬናዊ ስምኦን የጌታን መስቀል የተሸከመበት ቦታ

ሌላኛው ክፍል ቢሮና ለጌታ ፊቱን መጥረጊያ ሰጥታው የፊቱ ገጽ የተሳለበት ሥፍራ አንስቶ እስከ የጌታን ልብስ የገፈፉበትና የተከፋፈሉበት በእጀ ጠባቡም ላይ ዕጣ የተጣጣሉበት ድርስ ያለውን ይመለከታል።

- ምዕራፍ 6. ቢሮና (ስራጺታ) የጌታን ፊት የጠረገጭበት ቦታ፡- አንዳንድ አባቶች 12 ዓመታት ያህል ደፍ ሲፈሳት ቆይታ የጌታን ልብስ ጫፍ በመዳሰሷ የዳነችው ሴት ናት ይላሉ።

ምዕራፍ 7. የጎልጎታ መቃረቢያ


ምዕራፍ 8. የጌታችንን ስቃይ ሴቶች አይተው ያለቀሱበት ቦታ፡- በዚህ ቦታ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የሆኑ የመነኮሳት መኖሪያ አሉ።


ምዕራፍ 9. መስቀል ይዞ የወደቀበት (ወዲቀ ምድር ዳግማዊ)፡- ቦታው የኢትዮጵያ ገዳማት መግቢያ በር ነው።

ምዕራፍ 10. ልብሱን የገፈፉበት (ተዐርቆተ ልብስ)




የመጨረሻዎቹ የመስቀል ጉዞዎች መስቀል ተሸክሞ የተጓዛቸው ጉዞዎች አብቅተው በተሸከመው መስቀል ሊሰቀልበት የመዘጋጃው ምዕራፍ ነው። በመስቀሉ ላይ አስተኝተው በአምስት ችንካሮች ከቸነከሩበት አንስቶ ይቀጥልና  ዮሴፍ ሥጋውን አውርዶ በሐዲስ መቃብር የቀበረበት የጉዞው ማብቂያ ምእራፍ ይሆናል።






ምዕራፍ 11. ጌታን የቸነከሩበት (ተቀንዋ በቅንዋት)

ምዕራፍ 12. መስቀሉን ያቆሙበት ቦታ (መዊት ላዕለ መስቀል)

ምዕራፍ 13. ቅዱስ ሥጋውን ያወረዱበት ቦታ (አውረድዎ እምዕፀ)

ምዕራፍ 14. ቅዱስ ሥጋውን የገነዙበት ቦታ (ገነዝዎ በሰንዱናት)

ምዕራፍ 15. ቅዱስ ሥጋው የተቀበረበት ቦታ (ቀበርዎ ውስተ መቃብር ሐዲስ)

*ምንጭ ፡- ስምዐ ጽድቅ ልዩ ዕትም መጋቢት 20-24 ቀን 2002 ዓ.ም ማኅበረ ቅዱሳን*

*ሰሙነ ሕማማት ትራክት ደ/ሠ/መድኃኔዓለም ቤ/ክ ስብከተ ወንጌል ድሬዳዋ*